# በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ማዕ/ጎ/ሀ/ስ ለጎንደር ደብረ ኀይል ወደብረ ጥበብ በአታ ለማርያም ካቴድራል ሰንበት ትምህርት ቤት የተሰጠ

## የመንፈሳዊ ዕውቀት ኮርስ




አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው ካሣ

(የመጻሕፍተ ሊቃውንት፣ የመጻሕፍተ መነኰሳትና የመጻሕፍተ ብሉያት ትርጓሜ መምህር)


ሐምሌ ፲፪፣ ፳፻፲፫ ዓ.ም

## መንፈሳዊ ዕውቀት

ያቀ-ዐወቀ ከሚለው የግእዝ ግ ዕውቀት ይገኛል፡፡ ዕውቀት ማት ስለነገሮች ግንዛቤ መኖር ማለት ነው፡፡ ዐዋቂውን መሠረት በማድረግ የዕውቀት ዓይነቶች ሁለት ናቸው፡፡ እነዚህም፡-

- የባሕርይ ዕውቀት
- የጸጋ ዕውቀት

የባሕርይ ዕውቀት የሚባለው የልዑል እግዚአብሔር ዕውቀት ነው፡፡ ይህ በዘመን ብዛት የማይለዋወጥ ቋሚ ዕውቀት ነው፡፡ የጸጋ ዕውቀት የሚባለው ደግሞ ለፍጡራን ያላቸው ዕውቀት ነው፡፡ ከፈጣሪ የተሰጠ በመሆኑ የጸጋ ዕውቀት ይባላል፡፡ መላእክት፣ ሰዎች፣ ደማውያን ፍጥረታት ያላቸው ዕውቀት የጸጋ ነው፡፡ ለሰዎች ያላቸው የጸጋ ዕውቀት ደግሞ በሁለት ይከፈላል፡፡ እነዚህም፦

- አእምሮ ጠባይዕ
- አእምሮ መንፈሳዊ

አእምሮ ጠባይዕ ለሁሉም ሰው በተፈጥሮ የሚሰጠው ዕውቀት ሲሆን ክፉንና መልካምን ለመለየት ይጠቅማል፡፡ “አእምሮሰ ጠባይዓዊት ይእቲ ፈሊጠ ሠናይ እምእኩይ ዘአስተናበሮ እግዚአብሔር ልዑል ውስተ ጠባይዓቲነ” እንዲል (ማር ይስ.27፥1)፡፡ አእምሮ ጠባይዕ በተፈጥሮ ይሰጣል፣ በሞት ይለያል፣ በትንሣኤ ይመለሳል፡፡ አእምሮ መንፈሳዊ ትእዛዛተ እግዚአብሔርን በመጠበቅ በቅድስና የሚገኝ ዕውቀት ነው፡፡ የመንፈሳዊ ዕውቀት ግቡ ሰማያዊ ሕይወትን ተስፋ በማድረግ መንግሥቱን መውረስ ነው፡፡ መነሻና መድረሻውም በዚህ ዓለም ተጀምሮ መንግሥቱን በመውረስ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ማግኘት ነው፡፡ መንፈሳዊ ዕውቀት የሁሉም ነገር አስገኚ ለክሥተቶቹም መነሻ የሆነውን የእግዚአብሔርን ሥራ ይገልጻል፡፡ መንፈሳዊ ዕውቀት እስክንሞት አያበቃም፡፡ መጠየቅ የተሳሳተ ነገር ካለን እንድናርም ይረዳናል፡፡ በኦርቶዶክሳዊ እይታ የማንኛውም ዕውቀት ምንጭ እግዚአብሔር ነው፡፡ በተሰጠን የአእምሮ ጠባይዕ ዕውቀት ተመራምረን፣ ተምረን፣ አንብበን…ወዘተ የምናገኘው ዕውቀት ሳይንሳዊ ዕውቀት ነው፡፡ ሳይንሳዊ ዕውቀት ሥጋዊና ማኅበራዊ ኑሮን በማሻሻል ረገድ ትልቅ አስተዋጽ አለው፡፡

## ሳይንሳዊ ዕውቀት

ሳይንሳዊ ዕውቀት የሚገኘው በማየት፣ በመመልከት፣ በላብራቶሪ ምርምርና በመሳሰሉት ሲሆን ፍጥረታት እርስ በእርስ ያላቸውን ትስስር በማጥናትና በመሳሰለው ነው፡፡ በሳይንሳዊ እይታ የዕውቀት ግቡ የዚህን ዓለም ሕይወት ምቹ ማድረግ፣ ሥጋዊ ሕይወትን ወይም ኑሮን ማቅለል ነው፡፡ መነሻና መድረሻው በዚህ ዓለም ተጀምሮ በዚህ ዓለም ይጠናቀቃል፡፡ የሰው የዕውቀት ደረጃ ተለዋዋጭ ስለሆነ ሳይንሳዊ ዕውቀትም በሰው የዕውቀት ደረጃ የሚለዋወጥ ነው፡፡ ሳይንሳዊ ዕውቀት መነሻው እምነት ነው፡፡ አንድን ጥናት ለመጀመር የተወሰኑ ነገሮችን እውነት አድርጎ መቀበልን ይጠይቃል፡፡ ሳይንሳዊ ዕውቀት ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ያለውን በመላምት የሚናገር ሲሆን መንፈሳዊ ዕውቀት ግን ስለ ዓለም አፈጣጠር በእርግጠኝነት ይናገራል፡፡ ሳይንሳዊ ዕውቀት በጥቂት ናሙና ላይ ተመራምሮ ባገኘው ውጤት ሌላውንም ነገር እንዲህ ነው ብሎ የሚጠቀልል ሲሆን መንፈሳዊ ዕውቀት ግን ከፈጣሪ በተሰጠው ልክ ሁሉንም መርምሮ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የመጀመሪያውን ሳይንሳዊ ዕውቀት ከእናት ከአባቶቻችን እናገኛለን፡፡ ከቤተሰቦቻችን መረዳቶቻችን

ይዳብራሉ፡፡ ግንኙነቶቻችን ከቤተሰብ አልፈው ወደ ጎረቤት ሲሻገሩ እንደዚያው ዕውቀታችንም እያደገና እየሰፋ ይመጣል፡፡ መደበኛም ይሁኑ መደበኛ ባልሆኑ የዕውቀት ተቋማት ስንገባ ደግሞ ዕውቀታችን በጣም ይሰፋል፡፡ ሰው ለማወቅ መሪ ያስፈልገዋል፡፡ ሰው ለሰው መድኀኒቱ ነው እንዲሉ፡፡ ያለኝ ዕውቀት ይበቃኛል አይባልም፡፡ ጉድለት ሊኖረንና መስተካከል የሚገባው ነገርም ሊኖር ይችላልና፡፡ የሰው ልጅ ዕውቀትን በተለያየ መንገድ ማግኘት ይችላል፡፡ በመስማት፣ በማየት፣ በማንበብ፣ በአጠቃላይ፣ በስሜት ሕዋሳቶቻችን አማካኝነት ብዙው ይታወቃል፡፡ ለማወቅ ማንበብ ይገባል፡፡ ለማንበብ ደግሞ የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡

- ✓ ጊዜ መመደብ
- ✓ ማጣራት (ጥሩ መጻሕፍትን መለየት)
- ✓ መጻሕፍትን ይዞ መጓዝ
- ✓ አንባቢወፐችን ማቅረብ
- ✓ ለሌሎች ማንበብ

ማንበብ የሚከተሉት ጥቅሞች አሉት፡፡

- የአእምሮ ምግብ ነው (ስለሆነም የአእምሮ ጡንቻ ይጠነክራል)
- የአእምሮ ኀይል (የማገናዘብ ችሎታ) ይጨምራል
- የስሜት ብልህነት (የሌሎችን ስሜት መረዳት) መዳበር
- የዕውቀት መጨመር
- የትኩረት መሰብሰብ

## የንባብ ዓይነቶች

-ተግባራዊ ንባብ (functional reading)፡- ሥራን ለማከናዎን የሚጠቅም የንባብ ዓይነት ነው፡፡

-የማሻሻል ንባብ (developmental reading)፡- የንባብ ልምድን ለማዳበር የሚነበብ ንባብ ነው፡፡

-የመዝናኛ ንባብ (recreational reading)፡- ለመዝናኛ፣ ለማድነቅ የሚነበብ የንባብ ዓይነት ነው፡፡

## የንባብ ደረጃዎች

- እማሬያዊ ንባብ (reading for literal meaning)፡- የተጻፈውን መረዳት
- ፍካሬያዊ ንባብ (reading to make inference)፡- በዚህ የንባብ ደረጃ አንባቢው የተጻፈውን ብቻ ሳይሆን ጸሓፊው ማስተላለፍ የፈለገውን ለመረዳት ጥረት የሚያደርግበት ነው፡፡
- የምዘና ንባብ (reading to evaluate)፡- የጸሓፊው ድምፀት ያመጣውን ተጽእኖ መረዳት፣ ወገንተኝነት ካለ ማየት፣ እንዲሁም እውነታ እና አስተያየትን ለይቶ ማስቀመጥ፣ አሉታዊ ይዘት ኖሯቸው በአዎንታዊ መልክ የሚቀርቡ ጽሑፎችን መረዳት፣ መረጃዎችንና አስተያየቶችን ቀላቅለው የሚያቀርቡ ጽሑፎችን በሚገባ መገንዘብ ነው፡፡

## የንባብ ልምድ እንዲዳብር አስተዋጽ የሚያደርጉ አካላት

ቤተሰብ፣ ማሕበረሰብ፣ ትምህርት ቤት፣ ባህል፣ ግላዊ ጠባይና የመሳሰሉት ለንባብ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡ የንባብ ልምድ ባለበት ማሕበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች በአካባቢያቸው ያሉ አንባብያንን በመከተል የንባብ ባህልን ያዳብራሉ፡፡ አንድ ዓይነት ወይም ተቀራራቢ የአኗኗር ዘይቤ፣

የሥነ ምግባር መርሖዎች፣ የዕውቀት መለኪያዎች እና ርእዮተ ዓለም ያለው የሰዎች ስብስብ ማሕበረሰብ ይባላል፡፡ ንባብ በማሕበረሰቡ ውስጥ ያለው ቦታ፣ ለሚያነቡ ሰዎች ማሕበረሰቡ የሚሰጠው ደረጃ፣ ንባብን እንደ አስፈላጊ የሕይወት ተግባር ወይም እንደ ትርፍ ሥራ የሚመለከትበት ሂደት የንባብ ልምድ በሚኖረው ዕድገት ላይ ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ ባህል ሰዎች በዙሪያቸው ያለውን ማሕበራዊ እውነታ የሚረዱበት፣ የሚተረጉሙበት፣ የሚገልጹበትና ምላሽ የሚሰጡበት የጋራ የሆነ የዕውቀት ሥርዓት ነው፡፡ አንባቢ ሕዝብ ጠንካራና በአስተማማኝ ሁኔታ ያደገች ሀገርን መፍጠር ይችላል፡፡ አንባቢ ማሕበረሰብ በራስ መተማመኑ ከፍተኛ ነው፡፡ ንባብን የማያውቅ ትውልድ ዕውቀትን ጠብቆ ለማቆየት ይቸገራል፡፡ በአጠቃላይ በመንፈሳዊ እይታ አካል፣ ቋንቋ፣ ፍጥረታት፣ ማወቂያ ከእግዚአብሔር የተገኘ ሲሆን በሳይንሳዊ እይታ ደግሞ ዕውቀት በምርምር፣ በመጠየቅ፣ በትውፊት፣ በትምህርት፣ በመምህራን ይገኛል፡፡

## የዕውቀት ጥቅሞች

- አለማወቅን ለማወቅ (1ኛ ቆሮ.8፥2፤ ማር ይስ.7፥1)
- መልካም የሆነውን ከክፉው ለመለየት
- ራስን ለማወቅ (ማር ይስ.19፥3)
- የሰውን ኑሮ ለማሻሻል
- የጽድቅ ሥራን ለመሥራት (ያዕ.4፥7)
- ጠቢብ ለመሆን

## ራስን ማወቅ

ማንኛውም ሰው ማን ነኝ፣ ምንድን ነኝ፣ ከየት መጣሁ፣ ወዴትስ እሔዳለሁ፣ ያለሁበት ቦታና በዙሪያዬ ያሉት ነገሮች ምንድን ናቸው፣ ለምን ተፈጠሩ…ወዘተ የሚለውን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልገዋል፡፡ የዚህን ዓለም የሕይወት ጉዞ ስናስብ ከሁሉም በፊት መቅደም ያበት ራስን ማወቅ ነው፡፡ ራስን ማወቅ ማለት ለራሳችን ያለንን አመለካከት፣ የራሳችንን ጠባይ፣ ከሌሎች ሰዎች የሚለየንንና የሚያመሳስለንን ማንነት በመረዳት በዓላማ መኖር መቻል ነው፡፡ ራሱን የሚያውቅ ሰው ጠንካራና ደካማ ጎኑን ለይቶ ያውቃል፡፡ ራስን ማወቅ የሕይወት ግብን ለማስቀመጥ፣ የወደፊት የሕይወት አቅጣጫን ለመምራት አስፈላጊ ነው፡፡ ማንነትን መረዳትና አካባቢን መረዳት ራስን የማወቅ መገለጫዎች ናቸው፡፡

## ራስን የማወቅ መገለጫዎች

- ደካማና ጠንካራ ጎንን ለይቶ ለማወቅ
- ለራስ ሕይወት ሙሉ ኀላፊነትን መውሰድ
- ስለራስ ያለን አመለካከት አዎንታዊ መሆን
- በራስ መተማመን መጨመር
- ራስን ለማሻሻል መጣር
- የሚሔዱበትን መንገድ (ራእይ) ማወቅ
- ለዓላማ መሳካት መሥዋዕትነትን መክፈል

ራሱን የሚያውቅ ሰው ራሱን ይመራል፣ ራሱንም ያበቃል፡፡ ራስን መምራት ማለት በሕይወት ሂደት ውስጥ ራስን በመሆንና በማወቅ እንዲሁም ራስን በመግዛት ራእይን ማሳካት ነው፡፡ ራስን

ማብቃት የምንለው ደግሞ ሰው ባለበት የግንዛቤ፣ የዕውቀት እንዲሁም የክህሎት ሁኔታ ራሱን ከሌሎች ጥገኝነት መታደግ ሲሆን ይህም የራስ መተማመንን ይጨምራል፡፡

## በራስ መተማመን

በራስ መተማመን የራስን ዕውቀት፣ ክብርና ችሎታን በማወቅ ውጤታማ በሆነ መልኩ ነገርን እፈጽማለሁ ብሎ በራስ ላይ እምነትን መጣል ነው፡፡ ይህም ረድኤተ እግዚአብሔርን መሠረት በማድረግ የሚከናዎን ነው፡፡

## በራስ የሚተማመን ሰው መገለጫዎች

- ስለነገ ሲያስብ የሚታየው መልካም መልካሙ ነው፡፡
- ምክንያታዊ በመሆን ምን ይመጣልን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ አደጋን በመጋፈጥ ዓላማውን ለማሳካት የሚጥር ነው፡፡
- ራሱን በትክክለኛ መንገድ የሚወድ ነው፡፡

## በራስ መተማመንን እንዴት መገንባት እንችላለን?

- በራስ መተማመናችንን የሚሸረሽሩ ሐሳቦችን በማስወገድ
- አሉታዊ ሐሳቦችን ወደ አዎንታዊ በመቀየር (የሚወረወርብንን ድንጋይ መልሶ ከመወርወር ሕንፃ፣ ካብ በማድረግ ወደ ጥቅም መቀየር)
- ዙሪያን በጥንቃቄ መቃኘትና ክሂሎትን ለይቶ ማወቅ
- ሁልጊዜም ራስን መሆን
- ለራሳችን ድክመት እኛው ራሳችን ኀላፊነትን መውሰድ